# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 227 መስከረም 10 2005 ገጽ 1


ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች ላይ ያለ የመንግሥት ሥልጣን መያዝ ያለበት በነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒን የሕዝብ ምርጫ ብቻ መሆን አለበት ብሎ በጽኑ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል። ባለጉዳዩ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሩ ተዘግቶበት በሚደረግ ምርጫም ሆነ ምደባ የሚመጣ ሹመት ተቀባይነት የለውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለውጥን የሚለካው ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን ባለው አስተዋጽያ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በአስቸኳይ የተሰበሰበው የወያኔ ፓርላማ የሁለቱን አዳዲስ የወያኔ ሹመኞችን ምደባ ተቀብሎ የጠቅላይ ሚንስቴርነትና የምክትል ጠቅላይ ምንስቴርነትን ሥልጣን አጸደቀላቸው

የመለስ ዜናዊን ከዚህ አለም በሞት መለየት ተከትሎ እረፍት ላይ ከነበርበት ለሁለተኛ ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ የተጠራው የወያኔ ፓርላማ በትናትናው ዕለት መስከረም 11 ቀን 2005 የሃይለማሪያም ደሳለኝን ጠቅላይ ምንስቴርነትና የደመቀ መኮንን ምክትል ጠቅላይ ምንስትርነት ማጽደቁን በአገዛዙ ሥር ያሉ መገናኛ ብዙሃን በሰፊው ዘግበዋል።

የወያኔ ፓርላማ አፈጉባኤ የሆነው አባዱላ ገመዳ ምላተ ጉባዔው መሟላቱን ጠቅሶ ለአስቸኳይ ስብሰባው የተያዘውን 3 አጀንዳዎች በቅደም ተከተል ሲያስተዋውቅ ሁለቱ የጠቅላይ ምንስትሩንና የምክትሉን ሹመት ማጽደቅ እንደሆነና 3ኛው "የባንድራ ቀንን አስመልክቶ የቀረበውን ውሳኔ መመርመሮ ማጽደቅ " የሚል መሆኑን ሲገልጽ ለአስቸኳይ ስብሰባ ተብሎ እረፍቱን አቋርጦ እንዲሰየም በተጠራው ስብሰባ ላይ በ 3ኛ አጀንዳ ነት የተያዘው ስለ ባንድራ ቀን መወያየት ምን አጣዳፊ እንዳደረገው ለአብዛኛው ተስብሳቢ ግራ እንደገባው ከምንጮች የተገኘው መረጃ አረጋግጦአል።

ከአንድ የተቃዋሚ መቀመጫ በስተቀር በፓርላማ ውስጥ ያሉትን መቀመጫዎች ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠረው ወያኔ ኢህአደግ የቀድሞ መሪዉን ለመተካት በጠራው በዚህ አስቸኳይ ስብሰባ መገኘት ከነበረባቸው 547 አባላቱ መካከል የተገኙት 375 ብቻ መሆናቸው የብዙ ፖለቲካ ገምጋሚዎችን ትኩረት ስቦ አልፎአል።

180 አባላት የሚገኙበት የኢህአደግ ምክር ቤት ባለፈው ቅዳሜ የግንባሩ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር አድርጎ የሰየማቸው ሃይለማሪያም ደሳለኝና ደመቀ መኮንን በትናትናው ዕለት በሸንጎው ጠቅላይ ምንስትርነትና ምክትል ጠቅላይ ምንስትርነት ሆነው ሲሾሙ በፓርላማው ውስጥ የነበረው የተሰብሳቢው ስሜት እጅግ ቀዝቃዛ ሆኖ ተስተውሎአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በጭካኔያቸዉ ወደር የማይገኝላቸዉ የወያኔ ፖሊሶች ደሴ ዉስጥ የሙስሊሙን ህብረተሰብ በቆመጥ ሲደበድቡ የሚያሳይ ቪድዮ ለህዝብ ይፋ ሆነ

በአማራ ክልል ደሴ ከተማ ዉስጥ የሚገኙ የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ባልደረቦች ነፃነታቸዉና ሰብዓዊ መብታቸዉ እንዲከበርና በሠላማዊ መንገድ ጥያቄ ያቀረቡትን የእስልምና እምነት ተከታዮች በዱላና በሰደፍ ሲደበድቡ የሚያሳይ ቪድዮ ከኢትዮጵያ ሾልኮ ወጥቶ በኢሳት አማካኝነት ለ እይታ መብቃቱን ለማወቅ ተችሎአል።

ቪድዮዉን ቀንና ማታ ይከታተሏቸዉ ከነበሩ የወያኔ የድህንነት ሰራተኞች ደብቀዉ ለኢሳት ቴሉቪዥን ያስረከቡት አንድ የደሴ ከተማ ነዋሪ አንደተናገሩት ሙስሊሙ ህብረተሰብ በሠላማዊ መንገድ ላቀረበዉ የመብትና የነፃነት ጥያቄ ወያኔ የሰጠዉ የዱላና የሰደፍ መልስ አገዛዙ ሠላም ከሚባል ቃል ጋር በፍጹም እንደማይተዋወቅ ያሳያል ብለዋል። እኚሁ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የፈለጉ አገር ወዳድ ንግግራቸዉን በመቀጠል አረመኔዎቹ የወያኔ ካድሬዎች በአንድ በኩል ለሞተዉ መሪያቸዉ አልቅሱ እያሉን በሌላ በኩል ደግሞ የራሳቸዉን ተለጣፊ መጅሊስ ሊሾሙብን ይሯሯጡ ነበር ብለዋል።

ግለሰቡ የወያኔን ወንጀልና ጭካኔ የሚያሳየዉን ቪድዮ የአለም ህዝብ እንዲያየዉ ለማድረግ ካሰቡ የቆዩ ቢሆንም እስከዛሬ የዘገዩት ከከደረሰባቸዉ ድብደባ እስኪያገግሙ ድረስ መሆኑን የወያኔ ዱላና ሰደፍ ያረፈበትን እጃቸዉንና ግንባራቸዉን በማሳየት እንባ እየተናነቃቸዉ ታናግረዋል።

ፖልሲ በሰላማዊ ዜጋ ላይ የሚወስደውን ጨካኝና ዘግናኝ ድብደባ የሚያሳየው ቪዲዮ በኢሳት አማካይነት ከተሰራጨ ቦኋላ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን ያነጋገርናቸው ሰዎች ሁሉ አውራውን በሞት የተነጠቀው ወያኔ ገና ወዴት እንደሚሄድ እንኳ በውል ሳይገነዘብ እስከዛሬ በህዝብ ላይ የሚፈጽመውን ሰቆቃ አጠናክሮ ለመቀጠል መወሰኑ ይህንን አገዛዝ በሰላማዊ መንገድ መቀየር ይቻላል ብለው ለመስበክ ለሚሹ ሽንፈት ነው ይላሉ። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ግዜ

## ወንጀለኛዉ የወያኔ ፍርድ ቤት የአቶ አንዱአለም አራጌና የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ንበረት እንዲወረስ ትዕዛዝ አስተላለፈ

በዘረኝነት ላይ የተመሠረተዉና ህዝብን ለማጥቃት ብቻ የተቋቋመዉ የወያኔ ፍርድ ቤት መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት የሀሰት ክስ መስርቶ ባስቀጣቸዉ በአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ የአመራር አካል በነበሩት በአቶ አንዱአለም አራጌና እንዲሁም በጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ንብረት እንዲወረስ ትዕዛዝ ያስተላለፈ መሆኑን የግንቦት ሰባት ምንጮች ከአዲስ አበባ ባስተላለፉት ዜና ገለጹ። ይህ ከቤተ መንግስት በሚመጣለት ልዩ ትዕዛዝ ብቻ እየተመራ የሚፈርደዉ ፍርድ ቤት ህግን፤ ሰብዓዊነትንና ኢትዮጵያዊ የዜግነት ተቋርቋሪነትን ፈጽሞ ባላገናዘበ መንገድ ባስተላለፈዉ በዚህ የቂም በቀል ዉሳኔዉ በአቶ አንዱአለም አራጌ ስም የተመዘገበ አንድ መኪና በዉርስ ለመንግስት እንዲሰጥ ከማድረጉም በላይ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በስሙ ተመዝግቦ የሚገኝ ባለ አንድ ፎቅ ቤትና ከወላጆቹ በዉርስ የተላለፈለት ሌላ አንድ ቤት ወደ መንግስት ይዞታ እንዲዛወር አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ አሜሪካ ዉሰጥ የሚኖረዉንና በትርፍ ግዜዉ ወገኖቹን በጋዜጠኝነት የሚያገለግለዉን አቶ አበበ በለዉን ለማጥቃት አገዛዙ የጠነሰሰዉን ሴራ ከግቡ ለማድረስ ሂሊና ቢሱ የፌዴራል ፍርድ ቤት በአቶ አበበ በለዉ ባለቤት ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት እንዲወረስ አድርጓል።

አቶ አንዱአለም አራጌና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ባለትዳርና የንናንሽ ልጆች አባት መሆናቸዉ እየታወቀ ንብረታቸዉ ይህንን ባላገናዘበ መልኩ እንዲወረስ መደረጉ የፍርድ ቤቱ ዉሳኔ በአንድ በኩል የወያኔን ዘረኝነት አጉልቶ የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ለቤተሰብ፤ ለህበረተሰብም ሆነ ለአገር ምንም ደንታ የሌለዉ ግዑዝ ፍጡር መሆኑን ያሳያል ሲሉ ብዙዎች በፍርደት ቤቱ ዉሳኔ የተናደዱ ኢትዮጵያዉያን አስተያየታቸዉን በመስጠት ላይ ናቸዉ።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ ሰዓሊያን ማህበር ሥም ለሟቹ አምባገነን መለስ ዜናዊ መታሰቢያ ሃውልት መሰራቱ ይፋ ሆነ

በኢትዮጵያ ሰዓሊያን ማህበር ሥም ተሰርቶ ለዘረኛውና አምባገነኑ የቀድሞ ህወሃት ሊቀመንበር መለስ ዜናዊ መታሰቢያነት ተበረከተ የተባለው ይህ ሃውልት ወደ ላይ ሁለት ሜትር ከፍታ ያለው ሲሆን ሟቹ መለስ ዜናዊ የህዝብ ፍቅር የነበረውና የሰላም ምልዕክተኛ ለማስመሰል እጁን እያውለበለበ ሰላም ሲሰጥ የሚያሳይ ነው።

ይፋ እንደሆነው መረጃ ሃውልቱን ለማሠራት ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ እንደተደረገና መለስ ዜናዊ በህይወት ዘመኑ ላከናወነው መልካም ሥራ መታሰቢያነት በኢትዮጵያ ሰዓሊያን ማህበር የተበረከተ ነው ተብሎአል።

የማህበሩ ፕሬዝዳንት ስዩም አያለው ለወያኔው የፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሰጠ በተባለው መግለጫ መለስ በህይወት በነበረበት ወቅት ለሃገሩ ከሰራው ታሪክ አኳያ ሃውልቱ በብሄራዊ ሙዚየም ውስጥ እንዲቆም የማህበሩ ፍላጎት በመሆኑ ጥያቄው ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ቀርቦአል።፡

መለስ ዜናዊ ከዚህ አለም በሞት ከተለየ ወዲህ ላለፉት 21 አመታት ወያኔ በህዝባችንና በአገራችን ላይ በፈጸመው ወንጀል በአባሪ ተባባሪነት እንጠየቃለን የሚል ስጋት አዕምሮአቸው ውስጥ ተሰንጎ እረፍት እየነሳቸው ያሉ ግብረአበሮቹ በአገሪቱ ውስጥ አንድም ወንጀል እንዳልተፈጸመና በስህተትም ቢሆን የአንድ ንጹህ ዜጋ ደም እንዳላፈሰሰ በሚያስመስል ሙገሳና ውዳሴ የሰቆቃና ጭፍጨፋ ስትራቴጂስትና መመሪያ አመንጭ የነበረውን የቀድሞ መሪያቸውን ተክለሰውነት በመገንባት እራሳቸውን በማጽናናት ተግባር እንደተሰማሩ ግልጽ እየሆነ መጥቶአል የሚሉ በርካቶች ናቸው።

በብሄራዊ ሙዚዬም መቀመጡ ቀረበ ከተባለው ጥያቄ ግልጽ የሆነው የመለስ ዜናዊ ሃውልት ማሰሪያ ሙሉ ወጪ ስነ ጥበብን በሚደግፍ አንድ የግል ድርጅትና በማህበሩ እንደተሸፈነ የገለጸው የማህበሩ ሊቀመንበር በቀጣይነት በመለስ ዜናዊ ስም አደባባይ የሚሰየም ከሆነ ባለ አምስት ሜትር ከፍታ ያለው ሃውልት ለመስራት ዝግጁ መሆኑን አመልክቶአል።

ወያኔ ኢህ አደግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረበት ወቅት ደርግ ገንብቶት የነበረውን ትላልቅ ሃውልቶች እንዳፈረሰና በተለያየ ሥም በደርግ ዘመን ተሰይመው የነበሩ ጎዳናዎችና አደባባዮች ሥም ወዲያው መለወጣቸውን የሚያስታውሱ አስተያየት ሰጪዎች የመለስ አፍቃሪዎችም ነገ በህዝብ የሚመረጠው መንግሥት የሚያፈርሰውን ድንጋይ በመካብ የአገሪቱን ገንዘብ ከሚያባክኑ ሟቹን ጠቅላይ ምንስቴር ተማምነን ነው ለጎዳና ተዳዳሪነት የተዳረግነው ብለው በሽሙጥ የነገሩዋቸውን ሚስኪን ዜጎች ቢያቋቁሙበት እንደሚመረጥ መክረዋል።

# ርእሰ አንቀጽ

## ወያኔን የማስገደድ አሊያም የማስወገድ ትግላችን ተጠናክሮ ይቀጥላል!!!

በረከት ስምዖን በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብሎ ኃይለማርያም ደሣለኝና ደመቀ መኮንን የኢሕአዴግ ዋናና ምክትል ሊቀመናብርት ሆነው መመረጣቸውን ተናግሯል። ኃይለማርያም ደሣለኝ ደግሞ የተደረገው "ምደባ" መሆኑን በአጽንዖት ደጋግሞ ሲናገር ተደምጧል። "በምርጫ" እና "በምደባ" መካከል ስላለው ውስጠ ወይራ ለጊዜው እንተወው እና በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እናትኩር።

ኃይለማርያም ደሣለኝና ደመቀ መኮንን የህወሓት አባላት አይደሉም፤ የታላቋ ትግራይ ሪፑብሊክ እቅድ ሲነደፍም በቦታው አልነበሩም። የእነዚህ ሁለት ሰዎች የኢሕአዴግ ዋናና ምክትል ሊቀመናብርት ሆኖ መመረጥ እና በቅርቡም ጠቅላይ ሚኒስትርና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ሊሰየሙ የሚችሉ መሆኑ በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ የሚኖረው አንድምታ ምንድነው? የእነዚህ ሰዎች ወደ ፊት መምጣት በገዢዎች ቡድን ውስጥ የአስተሳሰብ ለውጥ መምጣቱን የሚያመለክት ነውን? እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ከየአቅጣጫው እየቀረቡ ነው።

በመለስ ዜናዊ የተመራው የትግራይ ገዢ ቡድን ሥልጣን እንደያዘ አንድ ማኀበረሰብ የሚገነባባቸው ሶስቱንም አውታሮች በመቆጣጣር በዘመናችን ተወዳዳሪ የሌለው ዘረኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ኢትዮጵያ ውስጥ አሰፈነ። እነዚህ ሶስቱ አውታሮች ፓለቲካ፣ ኢኮኖሚና ሲቪል ማኀበረሰቡ ናቸው።

በፓለቲካው ረገድ ቡድኑ ራሱ ህግ አውጭ፣ ህግ ተርጓሚ እና ህግ አስፈፃሚ በመሆን ሁሉንም መንግሥታዊ ሥልጣኖችን ተቆጣጠረ። በተለይም የመንግሥት የአስተዳደር መዋቅርን፣ መከላከያ፣ ደህንነትን እና የፍትህ ሥርዓቱን በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። በኢኮኖሚው ረገድ ኢፈርትንና መሰል ኩባንያዎችን አደራጅቶ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ። ሲቪሉ ማኀበረሰብን ለማስገበር ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስና የኢትዮጵያ እስልምና ምክር ቤት (መጅሊስ) ከመቆጣጠር ጀምሮ እስከ ገጠር መንደር ድረስ የወረደ የመቆጣጠሪያ መረብ ዘረጋ። "የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ" ማለት ይኸ ሁሉ ነው። ስለትግራይ ገዢ ጉጅሌ (ቡድን) ስንናገር የምናስበው ይህንን ሰፊ የአፈናና የብዝበዛ መረብ ነው።

አሁን መለስ ዜናዊ እንደ ግለሰብ ሞቷል፤ የገነባው ዘረኛ የአገዛዝ ሥርዓት ግን አለ። የመለስ ዜናዊ መሞት አገዛዙን የነቀነቀው ቢመስልም ሥርዓቱ የተገነቡበት ምሰሶዎች፣ ግድግዳና ጣሪያዎች ግን በቦታቸው እንዳሉ ናቸው። ለማስረጃም ያህል ዛሬም መከላከያና ደህንነት በወያኔ እንደተያዘ ነው። እንዲያውም በቅርቡ በተደረገው ሹመት ጦሩ ከቀድሞው የባሰ ወያኔያዊ እንዲሆን ተደርጓል። ከብርጋዴር ጀኔራልነት ወደ ሜጀር ጄኔራልነት እንዲያድጉ የተደረጉት ሶስቱም ከፍተኛ መኮንኖች የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው የሚያመለክተው ይህንኑ ነው። ከኮለኔልነት ወደ ብርጋዴር ጄኔራልነት ማዕረግ ካደጉት 34 ወታደራዊ መኮንኖች 22ቱ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው የሚያረጋግጠው ና ይህንኑ ነው። ሁሉም ተሿሚዎች የወያኔ አባላት ወይም ታማኝ ደጋፊዎች መሆናቸው ግልጽ ነው። በኢኮኖሚው ረገድ የታዩ መሻሻሎች የሉም፤ ዘረፋው እንደቀጠለ ነው። በቤተክህነትና በመጅሊስም ወያኔ የራሱን ሰዎች እንደገና ለማንገስ እየጣረ ነው። እስከ ገጠር መንደር የወረደው የወያኔ መረብ እንዳለ ነው። በዚህም በተጨማሪ አዲሶቹ ተሿሚዎች እየማሉና እየተገዘቱ ያሉት የመለስ ዜናዊ "ራዕይ" ስለማሳካት መሆኑ አጽንዖት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች ላይ ያለ የመንግሥት ሥልጣን መያዝ ያለበት በነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒን የሕዝብ ምርጫ ብቻ መሆን አለበት ብሎ በጽኑ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል። ባለጉዳዩ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሩ ተዘግቶበት በሚደረግ ምርጫም ሆነ ምደባ የሚመጣ ሹመት ተቀባይነት የለውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለውጥን የሚለካው ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን ባለው አስተዋጽዖ ነው።

ብአዴኖች፣ ኦህዴዶችና ደህዴዶች ራሳቸውን ከህወሓት ባርነት ነፃ የማውጣት ድፍረት ያላቸው ከሆነ፤ በህወሓት ውስጥም የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ያደረሰው እና ወደፊትም ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት የተገነዘቡ ሰዎች ካሉ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን አስተዋጽዖ ያላቸው ተጨባጭ ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርባቸዋል። የሚከተሉት ተግባራት ደግሞ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል።

1. መለስ ዜናዊ የገነባቸው የስለላና የብዝበዛ መዋቅሮችን ማፈራረስ፤
2. የመከላከያ ሠራዊትና የደህንነት መሥሪያ ቤት ከህወሓት ቁጥጥር ነፃ ማውጣትና ታማኝነቱ ለኢትዮጵያ በሆነ ሠራዊትና የደህንነት ተቋም መተካት፤ እና
3. በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ኃይሎችን ሁሉ የተሳተፉበት ነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒን ምርጫ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ለሽግግር ሥርዓት ቦታ መልቀቅ።

እስካሁን ከላይ በተዘረዘሩት የተግባር መስኮች ላይ ያየነው ፍንጭ የለም። የመለስ ዜናዊ በሞት መለየት ህወሓትን የጎዳ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ተገዶ ወደ ድርድር የሚመጣበት ደረጃ ግን ገና አልደረሰም። ስለሆነም ትግላችን ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ ቆርጦ መነሳት ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ "አልገዛም!" ማለት ይኖርበታል።

ብአዴኖች፣ ኦህዴዶችና ደህዴዶች እንዲሁም ህወሓት ውስጥ ለሕዝብና ለአገር ወገናዊነት ያላችሁ ብትኖሩ አሁኑኑ ከሕዝብ ጎን ብትቆሙ ራሳችሁን ታድናላችሁ፤ አገራችሁን ትጠቅማላችሁ። አለበዚያ ግን በተባበረ የሕዝብ አመጽ ወያኔ መወገዳችሁ አይቀርም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከሌሎች ድርጅቶ ጋር በመሆን ይህንን ትግል እየመራ ነው። ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ የናፈቀው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከግንቦት 7 ጎን ይሰለፍ!!! የቆምንለትን ሕዝባዊና አገራዊ ዓላማ እናሳካለን!!!

**መልካም አዲስ ዓመት!!!**

---

## በአስቸኳይ የተሰበሰበው የወያኔ ፓርላማ የሁለቱን አዳዲስ የወያኔ ሹመኞችን ምደባ ተቀብሎ የጠቅላይ ሚንስቴርነትና . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሃይለማሪያም ደሳለኝ ቃለማሃላውን ከፈጸመ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ባደረገው ኦፍሴላዊ ንግግር ለዚህ ሥልጣን ያበቃውን ባለውለታውን መለስ ዜናዊን ደጋግሞ በየደቂቃው ሲያሞካሽና ሲያወድስ ከመሰማቱም በላይ በየትኛውም መንግሥታዊ የሥልጣን ርክክብ ወቅት ተሰምቶ በማይታወቅ አምልኮአዊ ውዳሴ " ዘላለማዊ ክብርና ሞገስ ለታላቁ መሪያችን ይሁን " ሲል ተደምጦአል።

መለስ ዜናዊ ከዚህ አለም በሞት ከተለየ ወዲህ በኢህአደጎች እየተዘወተረ በመነገር ላይ ያለው "የመለስ ራ ዕይ አንተገብራለን " መፈክር በትናትናው የሃይለማሪያም ደሳለኝና ምክትሉ ደመቀ መኮንን ንግግር ተደጋግሞ ተስተጋብቶአል። መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት ህዝባችንን ሲያምታታበትና ድፍን አለምን ሲያሞኝበት የኖረው በሃሰት ላይ የተመሰረተ የኢኮኒሚ ዕድገትን እንቀጥልበታለን ያለው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ከሟቹ አለቃው ጉልበት በታች ሆኖ ሲጋት የኖረውን ሃሰተኛ የዕድገትና የልማት አሃዝ ሸምድዶ በአሥር አመት ውስጥ አገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እናሰልፋለን ሲል መደመጡ ብዙዎችን አስገርሞአል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የዘረጋውን ዘረኝነትና አድሎአዊነት አገር ውስጥ ሆኖ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ባለመቻላቸው ለነጻነታቸው ሲሉ መሳሪያ ያነሱትንና በህዝባዊ አመጽ ለውጥ ለማምጣት የሚንቀሳቀሱትን አገር ወዳዶች እንደሌሎች የቀድሞ አለቆቹ ሁሉ በጠላት መሳሪያነት የፈረጀው ሃይለማሪያም ደሳለኝ አገሪቱ ውስጥ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብት ተቋማት ግንባት በመልካም ጅምር ላይ ያለ በማስመሰል እንገፋበታለን ሲል ተደምጦአል።

ሃይለማሪያም ደሳለኝም ሆነ በትናትናው ዕለት አስቸኳይ ስብሰባ የደረገው የወያኔ ፓርላማ የአገሪቱን መጻይ ዕድል ሊወስን ስለሚችለው ሁሉ አቀፍ የፖለቲካ ድርድር ያሉት አንድም ነገር አልነበረም። በዚህም ምክንያት የሃይለማሪያም ደሳለኝ ካቢኔ ገና ከጅምሩ "የጉልቻ ቢለዋወጥ" አይነት መሆኑን ይፋ በማድረጉ ሥልጣን ላይ ምን ያህል ዕድሜ ሊኖረው እንደሚችል የሚወስነው ኢትዮጵያዊያን ለነጻነታችንና ለክብራችን የምናደርገው ወሳኝ ትግል እንደሆነ ሁሉም ይስማማበታል።

## ወንጀለኛዉ የወያኔ ፍርድ ቤት የአቶ አንዱአለም አራጌና የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ንበረት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ባልና ሚስት አንድ ናቸዉ የሚለዉን ሀይማኖታዊ መርህና ጋብቻ ህጋዊ ድጋፍ ይኖረዋል የሚለዉን አለም አቀፋዊ ህግ በመጣስ የተወሰነዉ ይህ ዉሳኔ የሁለቱን ቆራጥ ታጋዮች ቤተሰብ ለመበተንና ሌላዉንም ታጋይ ለማስፈራራት ሆን ተብሎ የተወሰደ የጭካኔና የቂም በቀል እርምጃ እንጂ የትክክለኛ ፍርድ ዉሳኔ አይደለም ሲሉ አንድ የእነ አንዱአለም አራጌን የፍርድ ቤት ዉሎ በየቀኑ ይከታተሉ የነበሩ የህግ ባላሙያ ለዝግጅት ክፍላችን ስልክ ደዉለዉ ተናግረዋል። አገራችንን የሚዘርፉና ህዝብን በየደባባዩ የሚገድሉ የወያኔ ጄኔራሎች ሁለትና ሦስት ትላልቅ ህንፃ እየሰሩ በሚንደላቀቁባት አዲስ አበባ ዉስጥ ሀቀኛ ዜጎች ሽብርተኛ ናችሁ እየተባሉ ንብረታቸዉ እንዲቀማ መደረጉ አጅግ የሚያሳዝን ነዉ ያሉት አኝህ የህግ ባለሙያ መብታችንንና ነፃነታችንን ፊት ለፊት ወጥተንና ከወያኔ ጋር ተጋፍጠን በሀይል ካላስከበርን ከዚህም በላይ ዉርደት ሊደርስብን እንደሚችል አስጠንቅቀዋል።

---

## እውነት ብቻ አርነት ታወጣችኋለች!!!

ኢትዮጵያችን ጥልቅና የረዥም ዘመን ታሪክ ባለቤት ነች።በብዙ ባእዳን ዓይንም ስትታይ ግርማዋ የሚያስፈራ ዜጎቿም የታላቅ አገር ልጆች ተብለው የሚከበሩ ነበሩ።አለመታደል ሆኖ ይህን ግርማዋን ጠብቃ ልትዘልቅ አልቻለችም። መሽቶ በነጋ ቁጥር ግርማዋ ደብዝዞ የርሃብና የችጋር መገለጫ ሁናለች። ሠላምም ርቋት የሰው ልጆች ደም በከንቱ የሚፈስባት የደም መሬት ሁናለች።ጨዋ ሰው ተዋርዶባት ነውረኞች በፍርድ ወንበር የተቀመጡባት ሥፍራ ሁናለች።

እስከ ዛሬ ከተነሱ አምባገነኖች መካከል የኢትዮጵያን  ግርማ ያጠፋ፤ዜጎቿንም ያዋረደ እንደ ህወሃት ያለ አልታየም። በኢትዮጵያችን ታሪክ ውስጥ ሃሰትና ሃሰተኞች የከበሩበት፤ እውነት እና እውነተኞች የተዋረዱበት እንደ ህወሃት ያለ ሥርዓትም አልታየም። እንደ ህወሃት መሠረቱን ጥላቻ፤ ጣሪያና ግድግዳውን ደግሞ ውሸት ያደረገ ድርጅት አልታየም። ይሄ ዘረኛ ድርጅት ቅንነት የሌለው ትእቢትና እኔ ብቻ ባይነት በልቡ የነገሰበት እና ውሸትን ባህሉ አድርጎ የኖረ ነው።መሪያቸው መለስ ዜናዊ በኃምሌ ወር ቢሞትም "ሃኪም የረዥም ግዜ ፈቃድ ሰጥቶ ነው፤ከእንቁጣጣሽ በፊት በጣም ፈጥኖ ወደ ሥራው ይመለሳል" እያሉ ህዝቡን ሲያታልሉት ቆይተዋል። ይሄ የህወሃት ባህል ነው። የጋናው ፕሬዝዳንት ሚሊ ሲሞቱ በማግስቱ ማረፋቸው ለህዝቡ ይፋ ተደርጎ በማግስቱ ምክትላቸው አገሪቷን እንዲመሩ ሙሉ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። በህወሃት ዘመን ኢትዮጵያዊያን የተናቁ እንጂ እንደ ጋናዊያን ክብር የሚገባቸው ስላይደሉ የመለስ ሞት ተደብቆ ከርሟል። ህዝብን መናቅ ደግሞ "ትግሬን" ነጻ እናወጣለን ብለው የተነሱ ቡድኖች አንዱ መገለጫ እና ባህላቸው ነው።

በአገራችን ውስጥ ህወሃትን አምኖ የሚደረግ ማንኛውም ጉዞ መጨረሻው ውርደት እንጂ ክብር ሊሆን እንደማይችል ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ውስጥ የተደረጉ ሙከራዎች ሁሉ ህያዋን ምስክሮች ናቸው።ጣሪያና ግድግዳውን በውሸት፤በማጭበርበር እና በዘረኝነት የገነባ ቡድን መኖሪያውን አፍርሶ እውነት ወዳለችበት ወደ ብርሃን ይመጣል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ብቻ ሳይሆን ህወሃት በዚያች አገር የፈፀመው እውነት እንዳይገለጥ ዘብ መቆምም ነው።ህወሃት በህዝብ ሥም የህዝብ ጠላት የሆነ ድርጅት እንጂ የሰለጠነ ፖለቲካ ለማካሄድ ግንዛቤውም ፈቃደኝነቱም ያለው ድርጅት አይደለም።

ህዝባችንን በመከፋፈልና ደካሞችን በትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞችና የሥልጣን ቱርፋት በመደለል የአገዛዝ ዘመናቸውን ለጭኑብን ከቻሉበት አንዱ በውሸት በተካነ አንደበታቸው በርካታ የህዋሆችን እየሸነገሉ መሆኑንም መካድ የለብንምም።" እነክን የሌለበት ምርጫ" እናካሂዳለን ብለው ካበቁ ቦኋላ ስንቱን እንዳሳሳቱና በመጨረሻው ውጤቱ ምን እንደነበረ ታይቶአል። በጋምቤላ፤ በኦጋዴን ፤ በአርሲ፤ በባሌ፤ በአዋሳ፤ በአርባ ምንጭ፤ በጎንደር፤ በድፍን ኦሮሚያ ወዘተ የሆነው ሁሉ እንዳለ ሆኖ አለም አቀፍህ ድርጅቶች መቀመጫቸው ባደረጉት አዲስ አበባ ውስጥ በአንዲት ጀንበር ብቻ በጠራራ ጸሃይ የተጨፈጨፈው ከሁለት መቶ በላይ ንጹሃን ዜጎችን ጉዳይ ምንጊዜም የሚረሳ አይሆንም። "የብሄሮችን እኩልነት እናረጋግጣለን" ብለው ሲያበቁ እነርሱ ብቻ የአገሪቷን መከላከያ፤ የደህንነት እና የኢኮኖሚውን ዋልታ ተቆጣጥረው እጅግ በሚያሳፍር ዝሪፊያ ውስጥ መዘፈቃቸው ሌላው አስከፊ ገጽታቸው ነው። እነርሱ ሁሉን ጨብጠውና ረግጠው በያዙት ኢትዮጵያ ውስጥ ከ11 ቢሊዮን ዶላር በላይ ከአገሪቷ በህገ ወጥ መንገድ ወጥቶ በውጭ አገራት ባንኮች ውስጥ ተደብቋል። ለዚህ ነው እንዲህ በውንብድናና በዝሪፊያ ላይ ከተሠማራ ቡድን ጋር ተደራድሮ ለሁሉም ዜጎች የምትሆን ኢትዮጵያን መፍጠር የሚቻል ያልሆነው።

ውድ ኢትዮጵያዊያን !

ህወሃት ከነ ነውሩ ከህግ በላይ ሆኖ ለሁሉም የምትሆን ኢትዮጵያን መፍጠር የሚቻል አይደለም።ለሁሉም የምትሆን ኢትዮጵያ እንድትፈጠር በቅንነት የሚሄድ እውነትንም ከህዝቡ የማይሰውር፤ በልቡም ለእውነት የቆመ፤ በአንደበቱም የማይሸነግል፤ በዜጎቹ ላይ ክፋት የማያደርግ፤ ወገኖቹንም የማይሳደብ፤ የድሆችን ገንዘብ የማይሰርቅ መሪ ያስፈልጋታል።የህወሃት መሪዎች እንዲህ ያለ ባህሪይ የላቸውም የእነርሱ መገለጫ ዝሪፊያ፤ ውሸት፤ ስድብ፤ ጭካኔ ነው። እነዚህ ቡድኖች በቀለኞች ናቸው። የመዘዙትን የበቀል ሰይፍ ወደ ሰገባው ሳይመለሱ የሚደረግ ድርድር በህዝብ ላይ መቀለድ ከመሆን ባሻገር የሚሰጠው ሌላ ትርጉም የለም። የእነዚህን ነፍሰ ገዳዮች ባህሪይ ያልተረዱና ከህወሃት ጋር ለመደራደር ፍላጎት ያላቸው ወገኖች ካሉ ግን አስቀድመው በዚያች አገር የህግ የበላይነት፤ ነጻ ፕሬስ፤ ነጻ ፍርድ ቤትና ነጻ የአገር መከላከያ ሃይል መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። በእኛ በኩል ግን ህወሃት  ይሄን ለማድረግ ተፈጥሮው ይፈቅድለታል ብለን አናምንም። ህወሃት ይሄን አደረገ ማለት የተከናነበው የውሸት ካባ ተገልጦ ከባዶ ስድሰት ተብሎ ከሚታወቀው እስር ቤት ጀምሮ እስከ ቃሊት ድረሰ የፈጸሙት ሰቆቃ እና ግድያ ተገለጠ ማለት ነው። ህወሃቶች የሚያስገድዳቸው ኃይል ሳይኖር እና በህይወት እያሉ ማንነታቸው እንዲገለጥባቸው ይፈቅዳሉ ብሎ መጠበቅ ጅልነት ነው።

ግንቦት ሰባት ከሁሉ አስቀድሞ በዚያች አገር እኩልነት፤ ፍትህ፤ ነጻነትና እውነተኛ ዴሞክራሲ ሰፍኖ ማየት ይፈልጋል። ድርጅታችን የቆመለትም የሚታገልለትም ዓላማና መዳረሻውም የሄው ነው። ህወሃቶች የነፈጉንን ነጻነታችንን እንዲሁ ይመልሱልናል ብለንም አናምንም። የግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ህወሃት ተለምኖ ሳይሆን ተገዶ ወደ ድርድር እንዲመጣ፤ ካልሆነም ከተቆናጠጠበት የስልጣን ወንበር ላይ አስገድዶ በማውረድ ከህግ በታች እንዲውል ለማድረግ ቆርጦ ተነስቷል። ምንም እንኳ መንገዱ ጠመዝማዛና ውጣ ወረድ የበዛበት ቢሆንም ለነጻነታችን ስንል ሁሉንም መንገዶች እንሄድባቸዋልን። ያዋጣናልብለን ያመነውን ዜዴ እንጠቀማለን። ውጊያችን በሁሉም ዘርፍ በሁሉም መንገድ ነው። ለነጻነታችን የማንከፍለው መስዋእትነት፤ የማንሄድበት መንገድ፤ የማንጠቀመው ዜዴ የለም።

ስለዚህ ጥሪያችን የአገሩ ጉዳይ የሚገደውና ፍትህ፤ እኩልነትና ነጻነት የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት አገር የሚናፍቀው ቅን ዜጋ ሁሉ የጀመርነውን ትግል ለማጠናከርና ብሎም ከፍጻሜው ለማድረስ ዛሬውኑ ይቀላቀለን የሚል ነው። ታግሎ ማሸነፍ እየተቻለ ከዳር ሆኖ ከንፈር መምጠጥ ወይም ስለ ችግሮች ማውራት ካለንበት ችግር ለአንድ እርምጃ ፈቀቅ እንደማያደርገን አጥብቀን ማሳወቅ የምንፈልገው ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ከማናገር የተለየ አቋራጭ መንገድ አለመኖሩን ሁሉም ተረድቶ እንዲረባረብ ነው። ሁላችንም እንደምንረዳው እስከዛሬ በአንድ ጥላ ሥር አለመሰባሰባችን አድክሞናል። አሁን ሁላችንም ድካማችንን የለየንበት ወቅት ነውና ኑና አብረን የነጻነቱን ጉዞ እንጓዘው። ተጋድሎውንም እንጋደል። የጊዜው አንገብጋቢ ጥሪ ይሄው ነው። ተባብሮ ለነጻነት የሚከፈለውን መስዋእትነ በጋራ መክፈል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የወያኔ ትምህረት ምንስቴር ለዩኒቨርስቲ መምህራን ሊሰጥ አስቦት የነበረውን  አገር አቀፍ ስልጠና መሰረዙን  አስታወቀ

በአዲሱ የወያኔ ምክትል ጠቅላይ ምንስቴእ የሚመራው የትምህርት ሚኒስቴር በቁጥር 7/ጠ-259/2311/04 በ 10/12/2004  ዓም በጻፈው ደብዳቤ ለዩኒቨርስቲ መምህራን ከመስከረም 10 እስከ 20 ቀን 2005 ዓም የሚቆይ አገራቀፍ ስልጣን ለመስጠት አቅዶ የነበረ ቢሆንም ይህን እቅዱን መሰረዙን ለዩኒቪርስቲዎቹ በተበተነ ደብዳቤ ማስታወቁን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከ ዘገባ ገለጸ።

ዩኒቨርስቲው የቪዲዮ ኮንፈረንሱን  ለማዘጋጀት በስድስት ኪሎ  እና በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ አዳራሾችን ቢያዘጋጅም፣ በዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት በዶ/ር አድማሱ ጸጋየ ፊርማ መስከረም 3 ቀን 2005 ዓም  በተጻፈው ደብዳቤ ስብሰባው ላልተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም ተዳርጓል።

ለስብሰባው መራዘም የተሰጠው ምክንያት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሚል ይሁን እንጅ የዩኒቨርስቲ መምህራን ለኢሳት ሰጡ በተባለ መረጃ አገዛዙ ውስጥ በተፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት ሳይሆን እንዳልቀረ ተገምቶአል።

ባለፈው ማክሰኞ መስከረም 8 9 ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን  ተሰጥቶ በነበረው ሥልጠና  ከትምህርት ጥራት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የሃይማኖት አክራሪነት የስልጠናው አጀንዳ ሆኖ እንደቀረበና በትናትናው ዕለት መስከረም 9 ደግሞ ኢህአዴግና መንግሥት በመተካካት ሂደት የደረሱበት ዕመርታ የውይይት መነሻ እንደነበረ ታውቆአል።

---

## በጭካኔያቸዉ ወደር የማይገኝላቸዉ የወያኔ ፖሊሶች ደሴ ዉስጥ የሙስሊሙን ህብረተሰብ በቆመጥ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መሳሪያ ያልታጠቁና ከፖለቲካ ሥልጣን ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለውን የእምነት ነጻነት ጥያቄያቸውን በሰላማዊ መንገድ ለማቅረብ እየባዘኑ ባሉ ሙስሊም ወገኖቻችን ላይ ወያኔ እየወሰደ ያለው የበረታ ጥቃት የጥቃቱ ሰለባ በመሆን ላይ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ሳይሆን መላውን የአገሪቱን ህዝብ ተስፋ የሚያስቆርጥና ለመራራ ትግል የሚያነሳሳ ነው ብለዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሌላ ዜና ላለፉት ሃያ አንድ አመታት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምህዳር ብቻዉን ተቆጣጥሮ የኖረዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የሀይማኖቱንም ዘርፍ ለመቆጠጠር ባለዉ ከፍተኛ ፍላጎት የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች መሪዎቻቸዉን አገዛዙ በፈለገዉ ቦታና መንገድ ብቻ እንዲመርጡ በማስገደድ ላይ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ምንጮች ገለጹ። በዚህም መሠረት በቅርቡ መሪዎቹን የሚመርጠዉ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ከፍላጎቱ ዉጭ መረዉን በየቀበሌዉ እየሄደ እንዲመርጥ በመደረግ ላይ ነዉ። እንደ ምንጮቻችን አባባል ወያኔ በፖለቲካዉ ዘርፍ በአምሳያዉ የፈጠራቸዉን የፖለቲካ ድርጅቶች በሀይማኖቱም ዘርፍ ለመድገም የቆረጠ ይመስላል። ሆኖም የወያኔ አገዛዝ የሙስሊሙ ህብረተብ ያነሳዉን የመብትና የነፃነት ጥያቄ በአግባቡ ካልመለሰ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እስከሞት ድረስ ለመታገል የቆረጡ መሆናቸዉን ላለፉት አስራአንድ ወራት ባሳዩት ጠንካራ የትግል መንፈስ አረጋግጠዋል።

---

## መለስ ዜናዊን በመተካት የኢህአደግ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ሆነው የተሰየሙት ኃይለማርያም ደሣለኝና ደመቀ መኮንንን ሹመት ለማጽደቅ አስቸኳይ የፓርላማ ስብሰባ ተጠራ

መስከረም 28 መደበኛ ሥራውን ይጀምራል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው የይስሙላው ወያኔ ፓርላማ ሰሞኑን የኢህ አደግ ምክር ቤት በሚቼ መለስ ዜናዊ ምትክ የግንባሩ ዋናና ምክትል ሊቀመንበር አድርጎ የመረጣቸውን ሃይለማሪያም ደሳለኝንና ደመቀ መኮንንን በጠቅላይ ምንስትርነትና በምክትል ጠቅላይ ምንስትርነት ለመሰየም አስቸኳይ ስብሰባ መጠራቱን የወያኔ ኮሚኒኬሽን መሥሪያቤት ምክትል ሃላፊ ሽመልስ ከማል አስታወቀ።

ከወር በላይ ተደብቆ የቆየው የዘረኛው መለስ ዜናዊ ዜና ህልፈት ለህዝብ ይፋ በሆነበት ነሃሴ ኢጋማሽ ላይ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ጠቅላይ ምንስቴር ሆኖ እንዲሰራ ሹመት ሰጥቶ የነበረው የምንስትሮች ምክር ቤት የሃይለማሪያምን ሹመት ለማስጸደቅ እረፍት ላይ የነበረውን ፓርላማ አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ሁሉም አባላቱ አዲስ አበባ ከተማ ከተሰባሰቡ ቦኋላ ምክንያቱ በውል ባልተገለጸ ሁኔታ ሰበሰባው ተሰርዞ የፓርላማ አባላቱ የመለስ ዜናዊን ለቅሶ ሲያደምቁ ሰንብተው ወደየመንደራቸው እንደተመለሱ በወቅቱ መዘገቡ ይታወሳል።

በነገው ዕለት ይካሄዳል ተብሎ የተጠራው አስቸኳይ የወያኔ ፓርላማ ከዚህ ቀደም የተጠራው አስቸኳይ ስብሰባ በምን ምክንያት እንደተሰረዘና የመለስ ዜናዊ ህመምና ህልፈት ለረጅም ጊዜ ለምን ለህዝብ ሳይገለጽ እንደቆየ ሥራ አስፈጻሚውን ይጠይቃል ተብሎ እንደማይጠበቅ ይታወቃል። ይልቁንም ለመለስ ዜናዊ የሂሊና ጸሎች አድርጎ የቲያትር ስብሰባውን እንደሚጀምርና በበረከት ስሞኦን ዋና ተዋናይነት ለኢህ አደግ ሊቀመንበርነትና ምክትል ሊቀመንበርነት የበቁትን ሁለቱን የመለስ ዜናዊ ታማኝ አገልጋዮችን ሹመት ተቀብሎ በጠቅላይ ምንስትርነትና በምክትልነት መሾማቸውን ሁሉም እጁን እንደቺቦ ወደላይ በመቀሰር ቡራኬ ሰጥቶ እንደሚበተን ይጠበቃል።

በሌላ ዜና ሃይለማሪያም ደሳለኝንና ደመቀ መኮንን ለሹመት ባበቃው ኢህአዴግ ስብሰባ ላይ የኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) በኢህአዴግ ሊቃነ-መናብርት ምርጫ ድምጽ ማጣቱ፤ በድርጅቱ ውስጥ ተቃውሞ መፍጠሩን ኢሳት በትናትና ምሽት ዘገባው ገልጾአል።

እንደኢሳት የመረጃ ምንጭ ባለፈው ሳምንት ኢህአዴግ ባካሄደው የሊቃነ-መናብርት ምርጫ ኦህዴድ ያቀረበው ዕጩ ድምጽ ተነፍጎ መውደቁ የድርጅቱን አንዳንድ አባላት አስኮርፏል። በዚህም ምክንያት የግንባሩ ስብሰባ ከተጠናቀቀ አጭር ቀናት ቦኋላ የኦህዴድ ስራ አስፈፃሚ አዲስ አበባ ውስጥ አስቸኳይ ዝግ ስብሰባ እንዲቀመጥ ተደርጎአል።

አዲስ አበባ ውስጥ የሚታተመው ሳምንታዊው የሰንደቅ ጋዜጣ ፤ የኦህዴድ የስራ አስፈፃሚ አባላት ስብሰባ ከኢህአዴግ የም/ቤት ስብሰባ በኋላ ወዲያውኑ እንዲካሄድ መደረጉ፤ የተለያዩ ወገኖችን ትኩረት እንደሳበና የስብሰባው አስፈላጊነት በተለይ ከኢህአዴግ የከፍተኛ አመራር መተካካት ጋር በተያያዘ በግንባሩ ውስጥ ኦህዴድ ተገቢውን ቦታ አላገኘም የሚሉ ብዥታዎችን ለማጥራት ታስቦ እንደሆነ ዘግቦአል።

በሌላ በኩል የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አለማየሁ አቶምሳ ቀደም ሲል የገጠመው የጤና መጓደል መሻሻል በማሳየቱ በእርሱ ቦታ ሌላ ሰው ለመተካት ይደረግ የነበረው ሩጫ እንደቆመ ለማወቅ ተችሎአል

ኢህ አደግ መለስ ዜናዊን እንዲተካለት የመረጣቸው ሃይለማሪያም ደሳለኝም ሆነ ደመቀ መኮንን ላለፉት 21 አመታት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በህዝባችንና በአገራችን ላይ የፈጸማቸውን ወንጀሎችና ደባዎች በሙሉ በጀሌነት ሲያስፈጽሙ የኖሩ በመሆኑ ምንም አይነት አገሪቱን ሊጠቅም የሚችል ለውጥ ለማምጣት ይችላሉ ተብሊኦ እምነት የሚጣልባቸው እንዳልሆነ የሚቀርቡ የህዝብ አስተያየቶች ቁጥር እየጨመረ መጥቶአል።

የድርጅቱን መሪ፤ ስትራቴጂስትና መሃንዲስ በሞት የተነጠቀው ወያኔ ኢህአደግ አገሪቱን በቀድሞ አለቃው መለስ ዜናዊ ራዕይ ለመምራት እያደረገ ባለው እንቅስቃሴ ቀደም ሲል የተጀመረውን አፈናና ወከባ በማጠናከር በሽብርተኝነት የፈጠራ ወንጀል ቃሊቲ የተወረወሩትን የጋዜጠኛ አስክንድር ነጋንና የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር አንዱአለም አራጌን ንብረት ለመውረስ የአገዛ ትዕዛዝ ማስተላለፉ ታውቆአል።

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተባለው የወያኔ ፍርድ ቤት በትናትናው እለት ባስተላለፈው ውሳኔ በወጣቱ የነጻነት ታጋይ አንዷአለም አራጌ ስም የተመዘገበው የቤት መኪናና ሃሳቡን በሰላማዊ መንገድ በመግለጹ ለሰለባ በተዳረገው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ስም የተመዘገበው ባለ አንድ ፎቅ ቤት እንዲታገድ ተደርጓል። በውጭ አገር ነዋሪ የሆነው የአዲስ ድምጽ አዘጋጅና ሃላፊ አበበ በለው ባለቤት ስም ተመዝግቦ ተገኝቷል የተባለ ባለ አንድ ፎቅ ቤትም እንዲታገድ የወያኔ ፍርድ ቤት ት ዕዛዝ መስጠቱ ተያይዞ በደረሰን ዜና ተገልጾአል።

## የወያኔን በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት እየተቃወመ ያለው የሙስሊም ህብረተሰብ ተቃውሞውን ነገ አርብ እንደሚቀጥልበት እያሰራጨ ባለው በራሪ ወረቀት አስታወቀ

ህወሃት መራሹ የወያኔ አገዛዝ በህዝባችን ላይ እያደረሰ ያለውን አፈና የሚቃወም እንቅስቃሴ በተለያየ የአገሪቱ ግዛቶች እየተጠናከረ በመምጣት ላይ ባለበት በአሁኑ ወቅት የሙስሊሙ ህብረተሰብ በሃይማኖቱ ጉዳይ የተፈጠረውን ጣልቃ ገብነት በመቃወም የጀመረውን ትግል በነገው ቀን ከጁማ ጸሎት ቦኋላ እንደሚቀጥል በአድስ አበባና በደሴ ከተማ ከተበተኑ በራሪ ወረቀቶች ለማወቅ ተችሎአል።

የወያኔ ቁንጮ የነበረው ዘረኛው መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት ሙሲሊሙ ህብረተሰብ ያነሳውን ጥያቄ ለአገዛዙ እንዲያቀርቡ የተመረጡትን መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት በፈጠራ ወንጀል እስር ቤት እንደወረወራቸው ሲታወቅ እስከ ዛሬ ድረስ ጉዳያቸው የይስሙላው ፍርድቤት ቀርቦ ውሳኔ እንዳልተሰጠበትና ለፊታችን ጥቅምት 2 ቀን 2005 ዓ.ም ፒያሳ በሚገኘው በአራዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊታይ የጊዜ ቀጠሮ መስጠቱ በርካታ የማህበረሰቡን አባላት አስቆጥቶአል።

እስር ላይ የሚገኙ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትንና የሙስሊሙን ጥያቄ ትደግፋላችሁ የተባሉ ኡላማዎችን ባለፈው ሳምንት አራዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቦ የነበረው የወያኔ አገዛዝ ተወካዮቹ የታሰረበት ህዝበ ሙስሊሙ ፍርድ ቤቱ ድረስ በመዝለቅ በአካባቢው የሚገኘው ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ድርስ ያለውን ሰፊ ቦታ በማጥለቅለቁ የተነሳ ግጭት እንዳይቀሰቀስ በመፍራት በትዕዛዝ ችሎቱ እንዲቋረጥ እንዳደረገና ከአሁን ቦኋላ ሂደቱ በዝግ ችሎት እንዲካሄድ ውሳኔ ማስተላለፉን ከውስጠ አዋቂ ምንጮች የተገኘው መረጃ አረጋግጦአል።

ሙስሊም ወገናችን ያነሳው ጥያቄ መንግሥት በሃይማኖቱ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት እንዲታቀብ ቢሆንም የእምነት ተቋሞችን በሥርዓቱ ደጋፊዎች ማስያዝ ሙያ ያደረገው ወያኔ የሙብት ጥያቄውን ለማፈን እየፈጸመ ካለው ጥቃት በተጨማሪ ከምዕመኑ ፈላጎትና ፈቃድ ውጪ ኡላማዎችን በቀበሌ ለማስመረጥ ካለፈው ሣምንት ጀምሮ ካድሬዎቹን በየከፍለ ከተማው፣ በየወረዳው በማሰማራት በያንዳንዱ ሙስሊም ቤት ላይ እየዞሩ ህዝብ በግዳጅ ወጥቶ በወረዳ የሚደረገው የመጅሊስ ምርጫ ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን ካርድ እንዲያወጡ እያስገደዱ መሆኑ ተደርሶበታል።

## የኢትዮጵያ ተስፋ ወጣቶች ድርጅት የተባለ የወጣቶች ንቅንቄ ህዝቡን ለትግል የሚያነሳሳ መልዕክት ያለው በራሪ ወረቀት መበተኑን አስታወቀ

የወጣቶቹ ንቅናቄ በሳምንቱ መጀመሪያ ላይ ወያኔ-ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሳቸው ያለውን በደሎች በመዘርዘር በበተነው ወረቀት ህዝቡ ይህን አስከፊ ስርዓት ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ውስጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረከት ጥሪ አስተላለፈ።

በወጣት ድርጅቱ በተበተነው በራሪ ወረቀት ላይ ወያኔ - ኢህአዴግ ለአገዛዙ እንዲያመቸው የኢትዮጵያን ህዝብ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በአካባቢና በሌሎችም ባገኛቸው ቀዳዳዎች ሁሉ እየተጠቀመ በመከፋፈል ሀገሪቱንና ህዝቡን ለከፋ አደጋ እያጋለጥ መሆኑን፣ በርካታ ዜጎችን ከኖሩበት ቀዬ በማፈናቀል መሬታቸውን ለውጪ ባለሃብቶች መቸብቸቡን ፣ በተሳሳቱ ፖሊሲዎቹ ህዝቡን በኑሮ ውድነት እየጠበሰው መሆኑንና ሌሎችንም ጉዳዮች አብራርቷል።

ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማጭበርበር ስለ ዴሞክራሲ ቢያወራም ወያኔ ከአፈጣጠሩ ጀምሮ ፍጹም ጸረ - ዴሞክራሲ እንደሆነ ይህም በ 1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት በግልጽ መረጋገጡን በወቅቱ የተገደሉና የቆሰሉ ዜጎችን ፎቶ ጭምር በማተም አሰራጭቷል።

የኢትዮጵያ ተስፋ ወጣቶች ድርጅት በተለይም ለመከላከያ ሰራዊት አባላት፣ ለፖሊስ ለደህንነትና ለወያኔ አገልጋይ ባለስልጣናት ጊዜው ሳያልፍ ከህዝቡ ትግል ጎን እንዲሰለፉ፣ ካለዚያ ቢያንስ ህዝቡን ከሚጎዳ እንቅስቃሴ እንዲታቀቡ መልእክት አስተላልፏል።

የድርጅታችን ዘጋቢ የወጣት ድርጅቱን እንቅስቃሴ አስመልክቶ ያነጋገራቸው ወጣቶች ይህ ጅምር እንቅስቃሴ እስከ ዛሬ የእኛ ዘመን ወጣት የህዝቡን በደል እያየ እንዳላየ ያልፋል እየተባለ ሲወቀስበት ለነበረው ጉዳይ ተግባራዊ ምላሽ በመስጠት የጀመረ በመሆኑ ደስተኞች ነን ፤ እኛም ከወጣቱ ድርጅት ጋር በመቀላቀል ህዝባችንን ከዘረኛውና በኢትዮጵያዊያን ጥላቻ ካበደው የወያኔ ስርዓት ለመገላገል ለሚደረገው ትግል የበኩላችንን አስተዋጽኦ እናበረክታለን ብለዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org